# ወያኔን ለምን ጠላሁ

***ይድረስ፡/-***
***ለፖለቲካ ኮማሪቶች፣ በህዝብ ስም ፖለቲካን ለማትረፊያነት መጠቀም ለሚፈልጉ ለሆድ አደሮችና አድረባዮች***

ወያኔን የምጠላው የድሮ ሚስቴን ስለሚመስለኝ ነው፡፡ የድሮ ሚስቴ ለጥቁርነት የተጠጋች ጠይም ናት» ተቀባብታ ስትወጣ ከቤት ውጭ የምትታወቀው በቀይነቷ ነው፡፡ እኔም ያገባኋት በቀይነቷ ነው ቀይ አለመሆኗ የገባኝ አንድ ቤት ውስጥ አብረን መኖር ከጀመርን በኋላ ነው፡፡አቤት እሷ ....! ስንት መልክ አላት መሰላችሁ ፤ ጠዋት አስቴርን ሆና ከሰዓት ከበቡሽን ትሆናለች ፤ ከበቡሽነቷን ስትለምዱት ደግሞ አቶ እርገጤን ሆና ታገኟታላችሁ፡፡ እናቴን ፤ አባቴን፤ አያቶቼንና ዘመዶቼን ሁሉ አትወድልኝም ......... የምትፈልገው የእሷን ጥፍር እንድከረክምላት ወይም ቅንድቧን እንድቀነድብላት ብቻ ነው፡፡ እኔንም ተንከባከባኝ አታውቅም ፡፡ ለኔ ቁራሽ እንጀራ በንፍገት እየሰጠችኝ በራችንን ለሚያንኳኩ ለማኞች ፤ ለሌሎች ጠያቂዎቿ እና ለአላፊ አግዳሚው ሁላ ሙሉ እንጀራ ከነወጡ ታቀርባለች፡፡ ከእኔ ጋር ከነቀሚሷ እየተኛች ለሌሎች ራሷን ገልጣ ትሰጣለች፡፡

በባልትና ጉዳይ ነካነካ ናት ተበድራ ስለገዛችው ስኳር መጣፈጥ ለማውራት አመት የማይበቃት ሽንኩርት መክተፍ ስለቻለች አፏን የምትከፍት ሴት ናት ፡፡ ቤት ውስጥ ነገረኛ ናት .......... ከቤት ውጪ በጎረቤቶቻችን እና በአልፎ ሂያጆች የሚወረወረው ድንጋይና ጠጠር ካደረሰብን ጉዳት በላይ እሷ የሰባበረችው መስታወት ይበልጣል ፡፡ በቤት ውስጥ ያለ ያልሰባበረችው ስብርብር ....... እንክትክት ያላረገችው መስታወት ካለ እንኳን ሰነጣጥቃ ለወደፊቱ እንዲሰባበር የተወችው ነው ፡፡ ብዙ ቅርሶቻችንን ሸጣ ስታበቃ የጋብቻ ወረቀታችን እንዳይቀደድ ታንገራግራለች ፡፡ ሀብትህን ባዶ አደርገዋለሁ ፤ የግል ልጆችህም ሆኑ የጋራ ልጆቻችን ብትንትናቸው ይወጣል እያለች ፍርሀትን ትፈጥርብኛለች ፡፡

እሷ ከላይኛው አንሶላ እኔ ከውስጠኛው አንሶላ እየተኛን አካላችን ሳይነካካ .... መንፈሳችን ሳይተቃቀፍ እሷ ሚስቱ (ባለቤቱ) ነኝ እያለች እኔ ሚስት እየናፈቀኝ በአንድ ቤት ውስጥ ኖርን ፡፡ አብሮ መኖራችንን ሳስታውሰው በአያቴ ቤት ግድግዳ ላይ በሚስማር የተመታ ትልቅ መስታወት ነበር ፡፡ የግድግዳ በዚያ ትልቅ ሚስማር ባይመታ ........ያ ትልቅ ሚስማር ባይገባበት የን ትልቅ መስታወት መሸከም ይችል ነበር ይሆንን እያልኩ ለብዙ ግዜ ራሴን ጠይቄአለሁ ፡፡ ከድሮ ሚስቴ ጋር ለብዙ ግዜ በአብሮነት የመቆየት ምስጢርም ባስገባችብኝ የፍርሀት ሚስማር ይመስለኛል ፡፡ አጋጣሚው ፈቀደና ከዛች ክፉ ሚስቴ ጋር ተለያየን ...... ከዚያ ጊዜ ወዲህ ወየኔን ሳየው እሷ ትዝ ትለኛለች ፡፡ ...አቤት መመሳሰላቸው ...አሁን አሁንስ የድሮ ሚስቴ ብዜ ሆና የመጣች እስኪመስለኝ ወያኔ ሚስቴን መሰለ፡፡

ወያኔ ቆሜለታለሁ የሚለውና ሌት ተቀን የህዝቡን ልብ ዝቅ በሚያደርግበት የቸከ ፕሮፖጋንዳ በሬዲዮ ቴሌቪዥን እና በተለያዩ ድህረ ገጾች የሚያሰራጨው አይነ ያወጣ ውሸት በውጭ ጌቶቹ ዘንድ ሊያሳየው የሚሻው ገጽታውና ተጨባጩ እውነታ ለየቅል መሆናቸው ፤ስለ ዲሞክራሲ ሰብዓዊ መብትና የህግ የበላይነት እያወራ በየቀኑ የሚያካሂደው አፈና ስየል እና

ግድያ ለቁጥር ማታከቱ ፤ ቆሜለታለሁ ድግሞም አስከብሬዋለሁ የሚለው የብሄር እኩልነት በየበዓላቱ ከአደባባይ ዳንኪራ እና ህዝቡን የመከፋፈያ መርዘኛ አላማውን ግብ ከማሳካት በዘለለ ለህዝቡ የፈየደው አንዳች ነገር አለመኖሩ ፤ በህገ-መንግስት ተብዬው የወያኔ ህገ ወንበዴ የሀይማኖት በመንግስት እና የመንግስትም በሀይማኖት ጣልቃ አለመግባት ተደንግጎ ሳለ ቤተ እምነቶችን በካባ ለባሽ ካድሬዎችና ሼኮች በመሙላት የሀይማኖት ነጻነትን ከመገፈፍ አልፎ እምቢኝ ለመብቴና ለዕምነቴ ያለውን ሁሉ የፀረ-ሽብር ህግ በሚለው የማፈኛና የማሸበሪያ ህጉ ሙሉ ለሙሉ የዕምነት ነፃነትን መግፈፉ ፤ የሰንደቅ አላማ ቀን እያለ በብዙ መቶ ሚሊዮን ብር እያፈሰሰ በግዳጅ ህዝቡን ሰልፍ እያስወጣ የኢትዮጵያ ህዝብ የማይቀበለውን ባንዲራ በግድ ማውለብለቡ ዓለም ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ሀቅ ነው፡፡

ይህ በደደቢት በጠላቶቻችን ተቀፍቅፎ የተፈጠረ ቡድን የኢትዮጵያን ታሪካዊ ፤ ባህላዊ ፤ ስነ-ልቦናዊና ልዩ ልዩ ዕሴቶቻችንን በማጠልሸትና ኢትዮጵያዊ ተቋማትንም በማፈራረስ ሌት ተቀን እየሰራ በዜና አውታሮቹና በተለያዩ ተቋማቱ ግን ሀገሪቱ ከገነት ይልቅ የተዋበች ፤ መብት ፤ፍትህ-ርትዕ፤ የህግ የበላይነት የሰፈነባትና ብሎም የዓለም ህዝብ ተምሳሌት እንደሆነች ይለፍፋል፡፡

ወያኔ አበው “የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ” እንዲሉ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት የሚለምን (ለሱዳን የተሰጠውን መሬትና መለስ ዜናዊ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ደብዳቤ ፅፎ ኤርትራን ማስገንጠሉ የሚታወስ ነው) የሀገሪቱን ጥቅም ለማስከበር ግዜ ግን ምክንያትን የሚደረድር የኢትዮጵያና የህዝቧ ጠላት ስለሆነ በተባበረ ክንድ ከጫንቃችን ላይ አሽቀንጥረን ልንጥለው ይገባል ፡፡ ለዚህ ደግሞ ፍርሀታችንንም አሽቀንጥረን ልንጥል ይገባል ፡፡ ፍርሀታችንን አውልቀን ጥለን አስመሳዮችንና አድርባዮችንም ጭምር ልንታገል ይገባል ፡፡ አንተ ከድሮ ሚስቴ ያፋታኸኝ ኢጋጣሚ ሆይ ......እባክህ ና ......እባክህ ና .......(ህዝባዊ አመፅ)!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!
ሀብታሙ ጀማል(ኑረምበርግ)
Habtamu Jemal
Nürnburg